ቅርቡ በቤተ ክርስቲያን ከተከሰተው ችግር ጋር በተያያዘ በርታ ምእመናንን ወደ ዝግጅት ክፍላችን ስልክ በመደወል፣ በአካል በመምጣት፣ ሕገ ቤተ ክርስቲያን በጉዳዩ ላይ ምን እንደሚል ጠይቀውናል፡፡ እኛም ቅዱስ ሲኖዶስ በ1991 ዓ.ም ካወጣው ሕገ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከጉዳዩ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን የተወሰኑ የሕጉን ምዕራፎች በመምረጥ አቅርበናል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ

አንቀጽ 5
የቅዱስ ሲኖዶስ ልዕልና /የበላይነት/
1. በመንፈስ ቅዱስ የሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ የመንበረ ሐዋርያት ወራሽ ስለሆነ በቤተ ክርስቲያኒቱ የመጨረ ሻው ከፍተኛ ሥልጣን ባለቤት ነው፡፡
2. ከማንኛውም የቤተ ክርስቲያኒቱ የሥልጣን መዋቅር ሁሉ የበላይ አካል ቅዱስ ሲኖዶስ ስለሆነ ሕጐችን፣ ልዩ ልዩ ደንቦችንና መመሪያዎችን የማውጣትና የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

አንቀጽ 6
የቅዱስ ሲኖዶስ ዓላማ

1. ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ አገልግሎቷም የተሟላ እንዲሆን ለማድረግ፣
2. ሃይማኖትና ቀኖና ቤተ ክርስቲያን እንዳይፋለስ ለመጠበቅና ለማስጠበቅ፣
3. ጥንታዊውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለመጠበቅና ለማስፋፋት፣
4. ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋትና ለማጠናከር፣
5. ወጣቶች ከአበው የተቀበሉትን ሃይማኖትና ሥርዓት ጠብቀው በትምህርትና በሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ ሰንበት ት/ቤትን ለማጠናከርና ለማስፋፋት፣
6. የሰው ዘር ሁሉ ከርሃብ፣ ከእርዛት፣ ከበሽታና ከድንቁ ርና ተላቆ በሰላምና በአንድነት በመተሳሰብና በመረዳ ዳት በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲኖር ማስተማርና መጸለይ፣

አንቀጽ 7
የቅዱስ ሲኖዶስ ሥልጣንና ተግባር
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡
1. ቅዱስ ሲኖዶስ ቤተ ክርስቲያንን በበላይነት ይመራል፣ ይጠብቃል፡፡
2. ሕገ ቤተ ክርስቲያን በሚፈቅደው መሠረት ሕጐችን፣ ደንቦችንና ልዩ ልዩ መመሪያዎችን ያወጣል፣ ያሻሽላል፡፡
3. የቤተ ክርስቲያኒቱን አጠቃላይ የምጣኔ ሀብትና የሙ ዓለ ንዋይ መመሪያዎችን /ፖሊሲዎችን/ ይወስናል፡፡
4. ዓመታዊውን በጀት ያጸድቃል ተግባራዊነቱንም ይቆጣጠራል፡፡
5. የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዳደራዊ መዋቅር እንዲሁም የጽሕፈት ቤቶችን ደረጃና ተጠሪነት ይወስናል፡፡
6. የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደርና አገልግሎት በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት እንዲመራ ያደርጋል፡፡
7. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እም ነት በአገር ውስጥና በውጭ አገር እንዲስፋፉ ያደር ጋል፡፡ ት/ቤቶችንም ያቋቁማል፡፡
8. የክርስቶስን ወንጌለ መንግሥትና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ያስተምራል፣ ያስፋፋል፡፡
9. በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር አዲስ የሀገረ ስብ ከት ጽ/ቤትና መንበረ ጵጵስና እንደ አስፈላጊነቱ ያቋ ቁማል፡፡
10. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከውጭ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያላትን ግንኙነት ያስፋፋል ያጠናክራል፡፡
11. በውጭ አገር በሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አህጉረ ስብከትና አጥቢያ ቤተ ክርስ ቲያን ለአገልግሎት የሚመደቡና እንደዚሁም በአገር ውስጥ የሚሰጠውን የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርት ተምረው የውጭውን ትምህርት መማር የሚችሉ ካህና ትን እየመረጠ እንዲላኩ ያደርጋል፡፡
12. ማንኛውም ሰው ቤተ ክርስቲያኒቱን ወክሎ ለሥራም ሆነ ለጉብኝት ወደ ውጭ አገር በሚላክበት ጊዜ ቅዱስ ሲኖዶስ እየፈቀደ ነው፡፡
13. ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሾሙ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ቅዱስ ሲኖዶስ በምልዓተ ጉባኤ እየወሰነ በቤተ ክርስ ቲያኒቱ ሕግ መሠረት እንዲመረጡና እንዲሾሙ ያደ ርጋል፡፡ እንዲሁም ሊቃነ ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን በየሀገረ ስብከቱና በተለያዩየሥራ ክፍሎች ይመድ ባል በበቂ ምክንያት ያዘዋውራል፡፡
14. በቋሚ ሲኖዶስ የሚያገለግሉ ጳጳሳትን በየሦስት ወሩ እየመደበ እንዲሠሩ ያደርጋል፡፡
15. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከፍ ተኛ ሥልጣን ላይ የሚመደቡትን
ሀ. የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ
ለ/ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ጠቅላይ ሥራ አስ ኪያጅ
ሐ/ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤቱ ም/ሥራ አስኪያጅ
መ/ የልማት ኮሚሽን ኮሚሽነር

ሠ/ የውጭ ጉዳይ መምሪያ ሓላፊ
ረ/ የልዩ ልዩ ሥራ ዘርፎች ቦርድ አባላት እየመረጡ እንዲሾሙ ያደርጋል፡፡
16. ቅዱስ ሲኖዶስ በየጊዜው በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች የሚቀርቡትን አጀንዳዎች ያጸድቃል እንደአስፈላጊነቱም ያሻሽላል፡፡
17. ቅዱስ ሲኖዶስ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡ ለጥፋተኞችና ለበደለኞችም ምሕረትና ይቅርታ የመስ ጠት ሥልጣን የቅዱስ ሲኖዶስ ነው፡፡
18. በዚህ ሕግ ባልተካተቱ በማናቸውም በቤተ ክርስቲ ያኒቱ ጉዳዮች ላይ ሁሉ ቅዱስ ሲኖዶስ የመወሰን ሥል ጣን አለው፡፡

አንቀጽ 8
የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት
1. በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት ፖትርያርክ፣ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ሆነው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አህጉረ ስብከትና በልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች የተሾሙ ሁሉ የቅዱስ ሲኖ ዶስ አባላት ናቸው፡፡
2. ከፓትርያርኩ ጀምሮ እያንዳንዱ ሊቀ ጳጳስ፣ ጳጳስና ኤጲስ ቆጶስ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው፡፡
3. የቅዱስ ሲኖዶስ አባልነት ዕድሜ ልክ ይሆናል፡፡
4. አንድ የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖትንና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን የሚያፋልስ ሆኖ ከተገኘ ከአባልነቱ ይሠረዛል፡፡
5. ይህም የሚሆነው በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ነው፡፡
6. በሃይማኖትም ሆነ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተከሰሰ የሲኖዶስ አባል በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ቀርቦ ራሱን የመከላከል መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
7. አንድ የሲኖዶስ አባል ስለራሱ ጉዳይ በሚታይበት ስብሰባ ላይ በአባልነት መገኘት አይችልም፡፡

አንቀጽ 9
የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ
1. የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ በፖትርያርኩ ሰብሳቢነት ይመራል፡፡ ትርያርኩ በልዩ ልዩ ምክንያት ጉባኤውን መምራት ባይችል ከአባላቱ መካከል እሱ የሹመት ቅድ ምና ያለውን አባት በመወከል ስብሰባው ሊመራ ይችላል፡፡
2. ከዚህ በታች ከተመዘገቡት በሦስት ምክንያቶች ካል ሆነ በቀር ትርያርኩ ርዕሰ መንበር ያልሆነበት የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ሊካሔድ አይችልም፡፡
ሀ/ ፓትርያርኩ በዕርግናና በጤና ጉድለት ምክንያት ጉባኤውን የሚመራ አባት መወከል ስላልቻለ፣
ለ/ የቤተ ክርስቲያንን እምነትና ቀኖና በተመለከተ የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ እንዲደረግ የሲኖዶሱ አባላት ሲጠይቁት ፈቃደኛ ሳይሆን ከቀረ፣
ሐ/ ስብሰባው ፓትርያርኩን የሚመለከት ጉዳይ ከሆነ በፍትሕ መንፈሳዊ መሠረት ይፈጽማል፡፡
3. ከዚህ በላይ በተዘረሩት ምክንያቶች ትርያርኩ ጉባ ኤውን መምራት ካልቻለ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በተ መረጡ የሹመት ቅድምና በአለው አንድ አባት ስብሰባው ሊካሔድ ይችላል፡፡

አንቀጽ 10
የቅዱስ ሲኖዶስ የስብሰባ ሥርዓት
1. ፍትሕ መንፈሳዊ በአምስተኛው አንቀጽ ቁጥር 164 በሚያዝዘው መሠረት ቅዱስ ሲኖዶስ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሒዳል፡፡ የስብሰባውም ጊዜ፣
ሀ/ የመጀመሪያው ጉባኤ በየዓመቱ ጥቅምት 12 ቀን
ለ/ የሁለተኛው ጉባኤ ትንoeሌ በዋለ በሃያ አምስተኛው ቀን /በርክበ ካህናት/ የሚካሔደው ነው፡፡
2. አስቸካይና ድንገተኛ ጉዳይ ሲያጋጥም፣
ሀ/ ቅዱስ ትርያርኩ ወይም ቋሚ ሲኖዶስ በሚያደ ርጉት ጥሪ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ሊካሔድ ይችላል፡፡
ለ/ ከጠቅላላው አባላት ከሦስት ሁለት እጅ የሚሆኑ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ምልዓተ ጉባኤ እንዲደረግ በጠየቁ ጊዜም ጥሪ ሊደረግና ስብሰባው ሊካሔድ ይችላል፡፡
3. የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ የሚባለው ከዓቅም በላይ የሆነ ዕክል ካላጋጠመ በቀር  መላው አባላት የተገኙ በት ጉባኤ ሲሆን ነው፡፡
4. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በሕመምና በልዩ ልዩ ከዓቅም በላይ በሆነ ምክንያት አንዳንድ አባላት ባይገኙ፣
ሀ/ ሃይማኖትንና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን በሚመለ ከት ጉዳይ ከጠቅላላው አባላት ከአራት ሦስት እጅ የተገኙ ከሆነ፣
ለ/ አስተዳደርን በሚመለከት ጉዳይ ከጠቅላላው አባ ላት ከሦስት ሁለት እጅ የተገኙ ከሆነ ነው፡፡
5. ቅዱስ ሲኖዶስ በማናቸውም ስብሰባ ላይ ውሳኔዎችን ሲያሳልፍ፣
ሀ/ አስተዳደርን የሚመለከት ጉዳይ ከሆነ ከተገኙት አባላት መካከል ከግማሽ በላይ በሆነ ድምፅ የተደገፈው ሐሳብ ያልፋል፡፡
ለ/ አንድን ጉዳይ ለመወሰን የአባላቱ ድምፅ እኩል በኩል ከሆነ ቅዱስ ትርያርኩ ያለበት ያልፋል፡፡
ሐ/ ሃይማኖትንና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከት ከሆነ በሙሉ ድምፅ ያልፋል፡፡

ምዕራፍ አራት
የኢትዮጵያ ትርያርክ
አንቀጽ 13
ስለ ቅዱስ ትርያርክ ምርጫ

1. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስትያን ት ርያርክ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግና ቀኖና በሚፈቅደው መሠረት ተመርጦ ይሾማል፡፡
2. ቅዱስ ሲኖዶስ ስለ ትርያርክ ምርጫ በሚወስነው ቁጥር መሠረት አስመራጭ ኮሚቴ ይቋቋማል፣
3. ለትርያርክነት የሚመረጡት ዕOEዎች ከሊቃነ ጳጳ ሳት ከጳጳሳትና ከኤጲስ ቆጶሳት መካከል ሲሆን ብዛታ ቸው ከሦስት ያላነሡ ከአምስት ያልበለጡ ይሆናል፡፡
4. አስመራጭ ኮሚቴው እOEዎችን ጠቁሞ ለቅዱስ ሲኖ ዶስ ያቀርባል፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግና ሥርዓት መሠ ረት ምርጫው እንዲካሔድ ይደረጋል፡፡
5. መራጮች የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት በሙሉ፣ የኢት ዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ፣ የየመምሪያና ድርጅት ሓላፊዎች፣ የጥንታውያን ገዳማት አበምኔ ቶች የአድባራት አስተዳዳሪዎች ከየሀገረ ስብከቱ ሰበካ ጉባኤያት በዕድሜ ከሠላሳ ዓመት ያላነሱ የካህናትና የምእመናን ተወካዮች እንዲሁም ዕድሜያቸው ከ22 እስከ 30 ዓመት የሆኑ የሰንበት ት/ቤት ተወካዮች ሲሆኑ ጠቅላላው በሰበካ ጉባኤው የሚወከሉት ከአንድ ሀገረ ስብከት አሥራ ሁለት ሆነው በሥጋወደሙ የተወሰኑ በሕገ ቤተ ክርስቲያን የጸኑ መሆን አለ ባቸው፡፡
6. የምርጫው አፈጻጸም ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡
7. የተመረጠው ትርያርክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማ ኖትንና ቀኖናዋን ሊጠብቅና አድልዎ በሌለው መልኩ ቤተ ክርስቲያኒቱን ሊያስተዳድር ቃለ መሐላ ይፈጽማል፡፡
8. ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ስለ ት ርያርክ ምርጫ ቅዱስ ሲኖዶስ ደንብ ያወጣል፡፡

አንቀጽ 14
የትርያርኩ የማዕረግ ስምና መንበር

1. ትርያርኩ ከተሾመበት ቀን ጀምሮ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ እገሌ ትርያርክ ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመን በረ ተክለሃይማኖት ይባላል፤ ስሙም በመላዋ የኢትዮ ጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጸሎት ይጠራል፡፡
2. ትርያርኩ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ለሚ ኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን መንፈሳዊ አባት ነው፡፡
3. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ት ርያርክ መንበር በአዲስ አበባ ከተማ በቅድስተ ቅዱ ሳን ማርያም ነው፡፡

አንቀጽ 15
የትርያርኩ ሥልጣንና ተግባር

1. ትርያርኩ በተሰጠው ሓላፊነት መሠረት ሃይማኖት ንና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ይጠብቃል፣ ያስጠብቃል፡፡
2. በዚህ ሕግ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ትርያርኩ የቅዱስ ሲኖዶስን ጉባኤ በሊቀ መንበርነት ይመራል፡፡
3. ፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ 5 እና በዚሁ ሕግ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 13 መሠረት ትርያርኩ ከቅዱስ ሲኖ ዶስ አባላት ጋር ሆኖ ኤጲስ ቆጶሳትን ይሾማል፣ እን ዲሁም ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው መመሪያ መሠ ረት ሲስማማበት ለብፁዓን ጳጳሳት የሊቀ ጵጵስና ማዕረግ ይሰጣል፡፡
4. በዚህ ሕግ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 15 መሠረት የተ መረጡትን የሥራ ሓላፊዎች ይሾማል፤ በቀደምትነትና በታሪክ የታወቁትን የታላላቅ ገዳማት አበምኔቶችና የከፍተኛ አድባራት አስተዳዳሪዎች በየሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ጳጳሳት እየተመረጡ ሲቀርቡለት የማዕረግ ስም እየሰጠ ይሾማል፡፡
5. ስለ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የመንግሥትን ፈቃድ ማግ ኘት በሚያስፈልግበት ጊዜ በቅዱስ ሲኖዶስ እያስወ ሰነ በተግባር ላይ ያውላል፡፡
6. ቅዱስ ትርያርኩ በዓበይት ጉዳዮች ላይ ሁሉ በቅዱስ ሲኖዶስ እያስወሰነ ይሠራል፡፡
7. በቅዱስ ሲኖዶስ የወጡ ሕጐች፣ የተላለፉ መመሪያዎ ችና ውሳኔዎች ሁሉ በተግባር ላይ መዋላቸውን ይከ ታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
8. በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወጡትን ሕጐችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን በፊርማው ያስተላልፋል፡፡
9. ከመንግሥታውያንም ሆነ መንግሥታውያን ካልሆኑ መ/ቤቶች ድርጅቶችና ግለሰቦች የሚቀርቡ ደብዳቤ ዎች ወይም አቤቱታዎችን ደረጃቸውን ጠብቀው በሕግ መሠረት ይፈጸሙ ዘንድ ለጠቅላይ ጽ/ቤት ያስተላልፋል፡፡
10. በውጭ አገር በሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አህጉረ ስብከት ለማገልገል ወይም የነፃ ትምህርት ለመማር የሚላኩ ካህናት በዚሁ ሕግ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 11 መሠረት ተመርጠው ሲቀርቡ እንዲላኩ ያደርጋል፡፡
11. ከውጭ የሚመጡትን እንግዶች በውጭ ጉዳይ ኃላፊ አቅራቢነት እየተቀበለ ያነጋግራል፡፡
12. ትርያርኩ በውጭ አገር በሚደረግ በማናቸውም ስብሰባ ላይ ለመገኘትና ጉብኝት ለማካሔድ በሚያስ ፈልግ ጊዜ ስለተልዕኮው ጉዳይ አስቀድሞ በቅዱስ ሲኖዶስና በቋሚ ሲኖዶስ ያስወስናል፡፡

አንቀጽ 16

የትርያርኩ ከማዕረግ መውረድ

1. ትርያርኩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ከተሾመ በኋላ የተቀበለውን ሓላፊነት በመዘንጋት፡-

ሀ/ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን የሚያፋልስ፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን የማይጠብቅ ቤተ ክርስቲያንን የሚያስነቅፍ ተግባር ፈጽሞ ከተገኘ፣

ለ/ በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ 5 ከቁጥር 172 እስከ 208 በተደነገገው መሠረት በደለኛ መሆኑ ከታመነበት፣

ሐ/ በቃሉ የማይገኝና በዚህ ሕግ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌ መሠረት በተሾመበት ቀን የፈጸመ ውን ቃለ መሐላ ያልጠበቀ በአጠቃላይ ታማኝነ ቱና መንፈሳዊ አባትነቱ በካህናትና በምእመናን ዘንድ ተቀባይነትን ያጣ ሆኖ ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚያስነቅፍ መሆኑ በትክክል ከተረጋገጠ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ከሥልጣኑ ይወርዳል፤ በምትኩም ሌላ ትርያርክ ተመርጦ ይሾማል፡፡

2. ከዚህ በላይ በተደነገገው መሠረት ከሥልጣኑ የተገለለ ትርያርክ በቀኖና ተወስኖ በገዳም ይቀመጣል፡፡

3. ከሥልጣን የተገለለው ትርያርክ በገዳም አልቀመ ጥም በቀኖናም አልወሰንም በማለት እምቢተኛ ከሆነ ተወግዞ ከቤተ ክርስቲያን አንድነት ይለያል፡፡

4. ትርያርኩ መንፈሳዊ ሥራውን በማካሔድ ላይ እያለ እሥራትና ግዞት ቢደርስበት ቤተ ክርስቲያኒቱ በቅዱስ ሲኖዶስ ትመራለች እንጂ ሌላ ትርያርክ አይሾምም፡፡

5. ከዚህ በላይ የተዘረዘረው ሁሉ ፍትሐ መንፈሳዊ በሚያዝዘው መሠረት ይፈጸማል፡፡

አንቀጽ 17

ዐቃቤ መንበረ ትርያርክ

1. ትርያርኩ በሞት ሲለይ ወይም በዚህ ሕግ አንቀጽ 16 መሠረት ከሥልጣኑ ሲወርድ ቅዱስ ሲኖዶስ በሹመት ቀደምትነት ካላቸው ሊቃነ ጳጳሳት መካከል በዕለቱ

ዐቃቤ መንበረ ትርያርክ መርጦ ይሾማል፡፡ የተተኪው ትርያርክ ምርጫም ይካሔዳል፡፡

2. የተተኪው ትርያርክ ምርጫ አፈጻጸም እንደጊዜውና እንደሥራው ሁኔታ እየታየ ከ40 እስከ 80 ቀን ባለው ጊዜ ይሆናል፡፡

3. የዐቃቤ መንበረ ትርያርክ ተግባር

ሀ/ ዐቃቤ መንበረ ትርያርክ ጊዜያዊ ጉዳዮችን ከቋሚ ሲኖዶስ ጋር እየመከረ ያከናውናል፡፡

ለ/ በትርያርኩ ምርጫ ጊዜም የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር ሆኖ ምርጫውን ያሰፈጽማል፤ እርሱ ግን ከምርጫው አይገባም፡፡